## ውድ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና የቀድሞ ምሩቃን፣

ይህን ጽሁፍ አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሆኜ የፃፍኩት ሲሆን፤ በአንድ በኩል ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ የኢንዱስትሪ እርምጃ ከፍተኛ የአሠራር መቃወስ እና የታላቁን የዩኒሳን መልካም ገጽታ፤ ዝና፤ታማኝነት ለማጥፋት ግርግር እየፈጠሩበት ሲሆን፤ ይህም በአገር ደረጃ ላይ ትልቅ ጉዳት እያደረሰ ነው። በሌላ በኩል ለዩኒሳ ተቋማዊ ቀጣይነት እና ስኬት በሌሎች ትልቅ ቁርጠኝነት እየተደረገ ነው።

ብዙዎቻችሁ የአገልግሎት ተጠቃሚዎቻችንን በተለይም ተማሪዎቻችንን የማገልገል ሀላፊነታችሁን ለመወጣት ወደ ተለያዩ ካምፓዎቻችን ለመንዝዝ ቅን፤ትጉህ እና ፍቃደኛ ሆናችሁ ብተቀጥሉም፣ ነገር ግን በመግቢያው ላይ በጥላቻ የተሞሉ ጠበኛ ባልደረቦች በመገኘታቸው ይህን እንዳታደርጉ እንደተከለከላችሁ ሙሉ በሙሉ አውቃለሁ፤ በተለይም  ወደ ፕሪቶሪያ እና ፍሎሪዳ ካምፓሶች በሚወስዱ መንገዶች።

ጉዳዩን ተባብሶ የቀጠለው ሲሆን ከነዚህም አስነዋሪ ድርጊቶች መካከል በየመንገዶች እና የመዳረሻ ቦታዎች ላይ ቆሻሻ እና የዛፍ ግንድ መጣል፣ ጎማ ማቃጠል፣ በመንገዶች ላይ ሹል መወርወር እና ግልጽ ማስፈራራት ናቸው።

ሆኖም ግን፣ በዚህ ሁሉ መካከል በዩኒቨርሲቲው የሚሰጡ አንዳንድ ቁልፍ አገልግሎቶች ያለማቋረጥ እንዲቀጥሉ መንገዶችን እና ዘዴዎችን የሚያፈላልጉ የዩኒሳ ሠራተኞች መኖራቸውን ባደረኳቸው ምልከታዎችና ዘገባውች ከልቤ አስተውያለሁ።

እንደሚታወቀው ባለፈው አርብ የ2022 የመጀመሪያ ሴሚስተር የመጀመሪያ ቀን የፈተና ነበር።የመጀመሪያው ቀን በአንፃራዊነት ጥሩ እንደነበር እና ለቀሩት የመጀመሪያ ሴሚስተር ፈተናዎች ሁሉም በሲስተሞች እንደሚሄዱ አስተያየት ስላገኘሁ በጣም ተደስቼ ነበር። አንዳንድ ያልተለመዱ ተግዳሮቶች በሚኖሩበት ጊዜ ፈተናውን እንዲመሩ የተቋቋሙት ቡድኖች መኖራቸውን እና እነዚህን በመለየት በፍጥነት ጣልቃ እንደሚገቡም ማረጋገጫ ተሰጥቶኛል።

እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ላይ ከሚተላለፉ የውሸት ዘገባዎች በተቃራኒ ማክሰኞ ግንቦት 10 ቀን 2022 የተከፈተው የእኛ ሴሚስተር ኦንላይን መተግበሪያዎች በጥሩ ሁኔታ እየሄዱ መሆናቸውን ማወቁም

አስደሳች ነበር። ይህ የማመልከቻ ደረጃ፣ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በክብር እና በድህረ ምረቃ ለተመረጡት ብቃቶች ብቻ የተከፈተ የዲፕሎማ ደረጃዎች፣ በሜይ 31፣ 2022 ይዘጋሉ።

በነዚህ ቦታዎች ለምትገኙ የስራ ባልደረቦች የዩንቨርስቲውን ስም በቁርጠኝነት እና በትጋት በመወከል ለቀጠሉት ፈታኝ ሁኔታዎች በኤክቲቭዩቲቭ ማኔጅመንት እና በተቀረው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ቢሆኑም በተለያዩ ቦታዎች ላሉ እና ስራቸውን እየሰሩ ለሚገኙ የስራ ባልደረቦቻችን ከልብ እናመሰግናለን።

ለትምህርታዊ አጀንዳ፣ ለሕቡንቱ መርሆዎች፣ ለፍትሃዊነት እና ለማህበራዊ ፍትህ እድገት በኢንዱስትሪ ተግባር ላይ ከሚገኙት የስራ ባልደረቦቻችን ጋር መደበኛ እና ህጋዊ ግንኙነትን ለመቀጠል ቁርጠኞች መሆናችንን እናረጋግጥልዎታለን። እኛ ግን ዩኒቨርሲቲዎቻችን ማህበረሰብን የሚያገለግሉ እና በእውቀት ግንባታ እና ስርጸት የማህበራዊ-ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ማእከል ሆነው ፤ምሁራን ተማሪዎችን የምናፈራባቸው ማህበራዊ ተቋማት መሆናቸውን እንደ አመራር ልንገልጽ እንወዳለን። ይህ ዩኒሳ የማይጸጸትበት ጥሪ እና ትዕዛዝ ነው። በመሆኑም ተቃውሞ የሚያደርጉ/ የስራ ማቆም አድማ የሚያደርጉ ባልደረቦች በሙሉ በዩኒቨርሲቲው ፖሊሲዎች እና በሀገሪቱ ህግጋት ውስጥ እንዲያደርጉ እንጠይቃለን። ለቀጣይ የኢንደስትሪ እርምጃ መፍትሄ ለማግኘት ቀጣይ ምክክር እናደርጋለን።

የአካዳሚክ አጀንዳዎችን መደገፍ የምትቀጥሉ ሁሉ መልካም ተግባራችሁን ዕንድትቀጥሉ ልንገልጽላችሁ እንወዳለን። ይህንንም እናስተውላላን። በዚህ ፈታኝ ጊዜ የዩኒሳን ባንዲራ ከፍ ብሎ በማውለብለብዎ ከልብ እናመሰግናለን።

*በትጋትዎ ይቀጥሉበት።*

*ከምልካም ምኞት ጋር*

*Puleng LenkaBula (ፕሮፌሰር)*

*ዋና እና ምክትል ቻንስለር*